በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ

# ወቅታዊ የአየር ጠባይ ትንበያ መጽሔት

ቅጽ፡3 ቁጥር፡2 ወቅት፡ ክረምት ግንቦት 2012

እ .ኤ.አ 2020 የበልግ ወቅት የአየር ጠባይ ግምገማና የክረምት ወቅት
የአየር ጠባይ አዝማሚያ




የክረምት ወቅት ዝናብ ሰጪ የሚቲዎሮሎጂ ገፅታ

# የተቋሙ ርዕይ፣ ተልኮ እና ዕሴቶች

## ርዕይ

የኢትዮጵያን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት የሚያግዝ ዓለም አቀፋዊ ደረጃውን የጠበቀ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም እውን ሆኖ ማየት፤

## ተልዕኮ

የሚቲዎሮሎጂ እና ተዛማጅ መረጃዎችን በመሰብሰብ በማደራጀት፣ በመተንተን የአየር ጠባይ ፣ የአየር ሁኔታ የአየር ጠባይ ለውጥና የአየር ብክለት በመከታተል እና በመተንበይ ለሀገሪቱ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት እንቅስቃሴዎች እንዲሁም ለህይወትና ንብረት ከአደጋ መጠበቅ እገዛ የሚያደርግ አገልግሎት መስጠት፤

## ዕሴቶች

- ጥራት ያለው አገልግሎት ፣ አስተማማኝ፣ ወቅቱን የጠበቀ፣ ውጤታማ፣
- ተደራሽና ደንበኛ ተኮር የአየር ጠባይ አገልግሎት
- ፈጠራ
- ሙያዊ ስነምግባር ፣ በቡድን መሥራት፣ ግልጽነት፣ ዕውቀትን ማካፈል
- ለወጣበት ዋጋ የሚመጥን ግልጋሎት

አድራሻ፡- ስልክ 0116615779/5512299
ፋክስ፡-0115517066/6625292
ፖ.ሳ.ቁ 1090
ኢሜይል፡-nmsa@ethionet.et;
nmsa.mafd@ethionet.et
ዌብሳይት፡ www.ethiomet.gov.et:www.meteo-ethiopia.net

www.masterprintaddis.net

## የብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ ስልጣንና ተግባር

ድርጅቱ ዓላማዎችን ከግብ ለማድረስ በአዋጅ ቁጥር 201/1973 ዓ.ም በተደነገገው መሰረት የሚከተሉትን ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

- የልዩ ልዩ ብሔራዊ የስራ እንቅስቃሴዎችና የልማት ፕሮግራሞችን ፍላጎት የሚያሟሉና የኢትዮጵያን የተፈጥሮ አካባቢዎች የሚወክሉ የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች በአገሪቱ ውስጥ ማቋቋምና ማካሄድ
- የሚቲዎሮሎጂ መረጃዎችን በሙሉ መሰብሰብ
- ኢትዮጵያ ተዋዋይ በሆነችባቸው የኢንተርናሽናል ስምምነቶች መሰረት የሚቲዎሮሎጂ መረጃዎችን መለዋወጥ
- የሚቲዎሮሎጂ መረጃዎችን ለመሰብሰብና ለማሰራጨት የሚያስችሉ የመገናኛ ዘዴዎችን በህግ መሰረት ማቋቋምና ማካሄድ
- የሚቲዎሮሎጂ መረጃዎችና የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ ውጤቶችን ማሳተምና ማሰራጨት
- ስለአስጊ የአየር ሁኔታ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ መስጠት ምክርና ትምህርት በሚጠየቅበት ጊዜ ለማንኛውም ሰው የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት መስጠት
- በአገሪቱ ውስጥ በማንኛውም ሰው የተሰበሰበውን ማናቸውንም የሚቲዎሮሎጂ መረጃ ማዕከላዊ በሆነ መንገድ ማከማቸትና ማስተዳደር
- የአገሪቱ አየር እንዳይበከል መቆጣጠርና የተፈጥሮ ሚዛኑም እንዳይዛባ ማድረግ
- ማንኛውም ሰው የሚቲዎሮሎጂ መረጃ ለመመዝገብና ለመሰብሰብ ሲጠይቅ አስፈላጊነቱን አመዛዝኖ መፍቀድ
- ሚቲዎሮሎጂን በሚመለከት በኢንተርናሽናል ደረጃ ተወስነው መንግስት ያፀደቃቸውን ስምምነቶች በስራ ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ
- ስለሚቲዎሮሎጂ ጥናትና ምርምር ማካሄድ ጠቃሚ ውጤቶችንም በስራ ላይ ማዋል
- ለሚሰጠው አገልግሎት የአገልግሎት ዋጋና ልዩ ልዩ ክፍያዎችን አግባብ ባለው የመንግስት መስሪያ ቤት አስወስኖ ዋጋ ማስከፈል
- ሚቲዎሮሎጂን የሚመለከት ማንኛውንም ስብሰባ፣ ጉባኤ ወይም ሴሚናር መንግስትን ወክሎ መሳተፍ
- ውል መዋዋል
- በስሙ መክሰስና መከሰስ
- ዓላማውን ለማሳካት የንብረት ባለቤት መሆን፣ ንብረት መያዝ፣ በመያዣ መስጠት፣ መለወጥ ወይም በማናቸውም ሌላ አኳኋን ማስተላለፍ